# ለእድገታዊ የንባብ ፈተና (DRA2)
# የወላጆች መመሪያ

DENVER PUBLIC SCHOOLS
Discover a World of Opportunity™

መመዘኛዎች ወይም ፈተናዎች ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለትምህርት ባለሙያዎች (አስተማሪዎች) ተማሪዎች የክፍል ደረጃቸውን እውቀት (ይዘት) ስለማወቅ አለማወቃቸው እና ለ21ኛው መ/ክ/ዘ ዝግጁ ሆነው ለመመረቅ ስለመቻል አለመቻላቸው ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። እያንዳንዱ ተማሪ በፈተና ውጤቱ መረጃ ተጠቃሚ ይሆናል፤ ምክንያቱም አስተማሪዎች ተማሪዎች የሚፈልጉትን ማወቅ ይችላሉና። መምህራንም ከተማሪዎች ፈተና ውጤት መረጃ ተጠቃሚ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም እንደትምህርት ባለሙያዎች የተማሪዎቻቸውን ልዩ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ይችላሉና።

## DRA2 ምንድን ነው?

የእድገታዊ የንባብ ፈተና (DRA2) ከመዋዕለ ህፃናት እስከ አምስተኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የማንበብና መጻፍ ደረጃቸውን ለማወቅ በመምህራን አንድ-ለ-አንድ የሚሰጥ ፈተና ነው። የዚህ የወረቀት እና የእርሳስ ፈተና ዋና ዓላማ የተማሪን የንባብ ችሎታ ደረጃን እና የተወሰኑ የጥንካሬ መስኮችን እንዲሁም በማንበብና መጻፍ (ሊትረሲ) ልማት ውስጥ ሊኖር የሚችል ፍላጎትን መለየት ነው።

DRA2 ከክፍል ደረጃቸው በታች በጣም ዝቅ ያለ አፈጻጸም ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ረገድ እና የማስተካከያ የንባብ እቅዶችን ለማዘጋጀት ከወላጆች ጋር አጋርነትን በመፍጠር ረገድ የኮሎራዶ ያንብብ /READ/ ደንብ የስቴት መስፈርቶችን ያሟላል።

## ልጄ የሚፈተነው/የምትፈተነው መቼ ነው?

የREAD ደንብ ፈተና ወቅቶች (ዊንዶውስ) በፎል እና በስፕሪንግ ውስጥ ለስድስት ሳምንታት ይቆያሉ። ት/ቤቶች ተፈላጊ ተማሪዎችን ለመመዘን መላው የፈተና ወቅት /window/ አላቸው። ልጅዎ አንድን ፈተና በክፍል ደረጃ እና በንባብ ደረጃ ላይ በመመሥረት በመላው የፈተና ወቅት ሳይሆን በየፈተና ወቅቱ (ዊንዶው) ቢያንስ በአንድ ቀን ውስጥ ከ20-40 ደቂቃ ይወስዳል። ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ሦስተኛ ክፍል ያሉ እና ከዝቅተኛው ገደብ በታች ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች በስቴት ሕግ መሠረት የንባብ ደረጃቸውን ለማረጋገጥ ከአንድ እስከ ሁለት ተጨማሪ ፈተናዎች ያስፈልጓቸዋል። ስለልጅዎ የፈተና ጊዜ ሰሌዳ ለማወቅ የልጅዎን ት/ቤት ያነጋግሩ።

### ኦገስት

| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ | አ | ቅ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | 31 | | | | | |

### ሴፕቴምበር

| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ | አ | ቅ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | | | |

### ኦክቶበር

| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ | አ | ቅ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1 | 2 | 3 |
| 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | 31 |

### ኤፕሪል

| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ | አ | ቅ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

### ሜይ

| እ | ሰ | ማ | ረ | ሐ | አ | ቅ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | 31 | | | | |

<u>መፍቻ ቁልፍ</u>

ከኬጂ እስከ 12ኛ በፎል

የመዋዕለ ህፃናት ተጨማሪ በፎል /Fall Kindergarten extension/

ከኬጂ እስከ 12ኛ በስፕሪንግ

## የልጄ ውጤት ምን ትርጉም ይኖረዋል?

የDRA2 ውጤት ልጅዎ ምን ያህል በንባብ ለውጥ/እድገት እንዳሳዩ/ች የሚያሳይ አንድ ማረጋገጫ ነው። ፈተናው በሚከተሉት ላይ በመመስረት የልጅዎን የንባብ ደረጃ ይለካል፡-

- የንባብ ተሳትፎ፡- ልጅዎ ከክፍል ውጭ ከመጽሐፍት ጋር ምን ያህል ጊዜውን ያሳልፋል/ታሳልፋለች።
- የአነባበብ ጥራት /Fluency/፡- ቃላትን እና ዐ. ነገሮችን ምን ያህል ጥሩ አድርጎ/ጋ ያነብባል/ታነባለች
- መረዳት፡- ልጅዎ የሚያነበውን/የምታነበውን ነገር ምን ያህል ይረዳዋል/ትረዳዋለች።

## እነዚህ ውጤቶች እንዴት ጥቅም ላይ ይውላሉ?

DRA2 መምህራን በመማር-ማስተማር ሥራቸው የሚመሩበት እና የሚያስተካክሉበት አንድ ጠቃሚ መረጃ ነው። የDRA2 ውጤቶች ተጨማሪ ሥራ የሚፈልጉትን የንባብ ክህሎቶች ለመለየት፣ ለተማሪዎች የንባብ ግቦችን ለማዘጋጀት፣ እና ልጅዎ ማንበብ ያለበትን/ባትን ያህል እያነበበ/ች መሆን አለመሆኑን/ኗን ለማወቅ ያገለግላሉ።

## ተጨማሪ መረጃ

በልጅዎ ትምህርት እና ለDRA2 ምዘናዎች (ፈተናዎች) ዝግጅት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ እናበረታታዎታለን። ልጅዎን በቤት ውስጥ ማገዝ ስለሚችሉባቸው መንገዶች የልጅዎን መምህር ለመጠየቅ ወደኋላ እንዳይሉ እባክዎ።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ወደstandards.dpsk12.org/assessments እንዲሄዱ እናበረታታዎታለን፡-

- የቴክኖሎጂ መመሪያ ለወላጆች
- መረጃ ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎች
- የኮሎራዶ ስቴት ግብዓቶች/አቅርቦቶች

ስለምዘናዎቹ ጥያቄዎች ወይም ሀሳቦች ካሉዎ፣ የልጅዎን ት/ቤት በቀጥታ ለማነጋገር ወይም የቤተሰብ የምርጫ ክልል /Constituency/ አገልግሎትን በ(720) 423-3054 ደውለው ለማነጋገር ወደኋላ አይበሉ።